የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ
The Holy synod of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church

No 2090/2015
Date 05/01/2015

**በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ። አሜን!**

***"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።"***
***(መዝሙር 67፥31)***

**በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በባልቲሞር፥ ሜሪላንድ አሜሪካ በሚገኘው መካነ ሰላም ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከሚያዝያ ፳፩-፳፫ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም. (April 29–May 1, 2015) ድረስ በቅዱስነታቸው አባታዊ ቡራኬ የተከፈተው ፵፩ኛው መደበኛ የርክበ ካህናት ጉባኤ ላይ የተሰጠ መግለጫ፤**

ጥንታዊት፥ ሐዋርያዊትና ብሔራዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ዘርፈ ብዙ መንፈሳዊና ማኅበራዊ እንዲሁም ታሪካዊና ባሕላዊ አስተዋጽዖ ያበረከተች ታላቅና ባለውለታ ቤተ ክርስቲያን መሆኗ ይታወቃል። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መቼም የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ ቀኖና መሠረት የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሉዓላዊ አካል የሆነው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያናችንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት አስመልክቶ እንዲሁም በወቅታዊው የአገራችን ጉዳይና በመላው ዓለም በስደት ተበትኖ በሚገኘው ሕዝባችን አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ሰፊና ጥልቅ ውይይት በማድረግ ከዚህ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ በጋራ አውጥቷል።

1ኛ/ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚታወቀው በኔሮን ቄሣር ዘመነ መንግሥት ያለ አንዳች ፍርሃት በድፍረት ሃይማኖተ ወንጌልን መስክሮ በሮም አደባባይ አንገቱን ለሰይፍ ስለት የሰጠው ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ "መኑ የኀድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ፥ ሕማምኑ፥ ምንዳቤኑ፥ ተሰዶኑ፥ ረኀብኑ፥ ዕርቃንኑ፥ መጥባሕትኑ፥ ጻዕርኑ፥ ... በእንቲአከ ይቀትሉነ ኵሎ አሚረ፥ ወኮነ ከመ አባግዕ ዘይጠብሑ፤ የክርስቶስን ፍቅር ማን ያስተወናል? ሕማም ነውን? መከራ ነውን? ስደት ነውን? ረኃብ ነውን? መራቆት ነውን? ሾተል ነውን? ጭንቅ ነውን? ... አንተን ስላመንን ዘወትር ይገድሉናል፥ እንደሚታረዱ በጎችም ሆነናል" (ሮሜ 8፥35-36) ሲል በአጽንዖት ተናግሯል። በዚህም ሐዋርያዊ ቃል መሠረት በቅርቡ በሊቢያ ምድር በቀናች ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው አንዳችም ሳያወላውሉ ጸንተው በመቆማቸው ምክንያት ራሱን 'አይሲስ' እያለ በሚጠራው አሸባሪ ቡድን እጅግ አሰቃቂና ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ የታረዱትንና በጥይት ተደብድበው እውነተኛ የሃይማኖት አርበኞች ለመሆን በጸጋ የታደሉትን የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችንን ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ **"ሰማዕታተ ኢትዮጵያ በምድረ ሊቢያ"** ወይም **"የኢትዮጵያ ሰማዕታት በሊቢያ ምድር"** ተብለው እንዲጠሩ በአንድ ድምፅ ወስኗል።

2ኛ/ ጥምቀተ ክርስትና ሳይፈጸምላቸው ከክርስቲያኖች ጋር አብረው በክርስቶስ ስም ሰማዕትነትን የተቀበሉ በሰማዕትነት ያፈሰሱት ደም ጥምቀት እንዲሆንላቸው በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፫ ቁጥር ፺፻፵፩-፺፻፵፪ ላይ "ያልተጠመቀ ሰው ልቡ አይዘን፥ ስለ ክርስቶስ የተቀበለው መከራ የተመረጠ ጥምቀት ይሆንለታልና። የሞቱን ምሳሌ በተቀበለ ጊዜ በጌታ አምሳል ሞቷልና፥ ሁለት ልብ አይሁን። እነርሱ ቢገድሉት እርሱም ቢገደል ይጸድቃል፥ በደሙ ተጠምቋልና" ተብሎ በተገለጸው የቅዱሳን አበው ድንጋጌ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰማዕታት አድርጋ እንደምትቀበላቸው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ይገልጻል።

3ኛ/ እነዚህ ሰማዕታት ከአምላካችን ከልዑል እግዚአብሔር የሰማዕትነትን ክብርና ሰማያዊ የድል አክሊል ያገኙ፥ ከቅዱሳን ሰማዕታት ማኅበር የተደመሩ ስለሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ ጸጋቸው ከኃዘኗ ትጽናናለች። እነዚህን ሰማዕታትን ዘወትር የምታስበውም እነርሱን ያከበራቸውን፥ ወደ ሰማዕትነት የመራቸውን፥ በቀናች ሃይማኖት አጽንቶ፥ በገድል ያበረታቸውን ልዑል እግዚአብሔርን በማመስገን ነው። በመሆኑም ሰማዕታተ ኢትዮጵያ በምድረ ሊቢያ በሰማዕትነት ያረፉበት ቀን በቤተ ክርስቲያናችን የመታሰቢያ በዓላቸው ሆኖ በየዓመቱ እንዲከበርና ዜና ገድላቸውም በስንክሳር እንዲዘከር ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል።


4127 Redwood Rd. Oakland CA 94619 Tel: (510) 530 3681

4ኛ/ በምድረ ሊቢያ በሰማዕትነት ላረፉትና የቤተ ክርስቲያናችን ብሩሃን ከዋክብት ለመሆን ለበቁት ሰማዕታት ወላጆችና ቤተ ሰቦች ሁሉ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰማውን ልባዊና ጥልቅ ኃዘን እየገለጸ **"የሰማዕታት ደም የቤተ ክርስቲያን ዘር ነው"** በሚለው የቅዱሳን አበው ብሂል መሠረት እኒህ ውድ ወገኖቻችን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው የከፈሉትን ከፍተኛ የሕይወት መሥዋዕትነትና በክርስቲያናዊ ዓላማ ጽናታቸውም የተቀዳጁትን ዘላለማዊ የድልና የሕይወት አክሊል በማሰብ እንድትጽናኑ በአክብሮት ያሳስባል።

5ኛ/ በሊቢያ ለተሠዉት ሰማዕታት ወላጆችና ቤተ ሰቦች አስፈላጊውን የገንዘብና የሞራል ድጋፍ ለመስጠት፥ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በስደትና በመከራ ፈታኝ በሆነ የሕይወት ጉዞ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ሕዝበ ክርስቲያኑን በማስተባበር በአስቸኳይ ለመታደግ እንዲቻል፥ እንዲሁም በገዛ አገሩ ላይ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥሮ፥ ነጻነቱ ተገፎና ሰብአዊ መብቱ ተጥሶ በአስከፊ ሁኔታ ላይ የሚገኘው ሕዝባችን ከምንጊዜውም በበለጠ ከአገሩ ወጥቶ እንዲሰደድ፥ በበረሃ ወድቆ፥ በባሕር ሰጥሞ እንዲቀር ያስገደደው ዋነኛው ምክንያት እንዲሁም ለቅዱስ ሲኖዶስ ስደት በታሪክ ተጠያቂ የሆነው አካል አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ሥርዓት በመሆኑ ለዚህ ብሔራዊ ችግር ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የውጭ አገር መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም ከሰብዓዊ መብትና የሲቪክ ተቋማት ጋር በቅርብ የሚሠራ፥ በሊቀ ጳጳስ የሚመራ ከካህናት፥ ከምእመናንና ከሰንበት ት/ቤት ወጣቶች የተውጣጣ ግብረ ኃይል (Task Force) ተቋቁሞ ሥራውን በአስቸኳይ እንዲጀምር ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በአንድ ድምፅ ወስኗል።

6ኛ/ በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አዘጋጅነት ቀዳሜ ሚያዝያ ፳፬ ቀን ፪፻፯ ዓ.ም. (May 2, 2015) በታላቅ መንፈሳዊ ድምቀት በሚከበረው የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፳፯ኛው በዓለ ሢመትና ሲኖዶሱ በቅርቡ የገዛው የመንበረ ፓትርያርክ ሕንፃ ምረቃ በዓል ላይ ቅዱስነታቸው ለቅዱስ ሲኖዶስ በሰጡት አባታዊ ማሳሰቢያ መሠረት በደቡብ አፍሪካ፥ በዓረቡ ዓለም፥ በየመንና በሊቢያ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች ይልቁንም ደግሞ በሜዲትራኒያን ባሕር ሰጥመው፥ በእሳት ተቃጥለው፥ በሰይፍ ታርደው፥ በጥይት ተደብድበው በግፍ የተገደሉት ውድ ኢትዮጵያውያን ልጆቻችንና ወገኖቻችን በጋራ እንዲታሰቡበት ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል።

7ኛ/ በመላው ዓለም በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በጋራ እንዲመሩበትና እንዲተዳደሩበት በጥር ወር ፪፻፯ ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ የወጣውና ለአህጉረ ስብከቶችና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የተሠራጨው ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሥራ ላይ እንዲውልና በአፈጻጸሙ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ሲኖሩ በቦታው የሚገኙ ብፁዓን አባቶች፥ ካህናት፥ የሰበካ ጉባኤ ወይም የአስተዳደር ቦርድ አባላትና ምእመናን በጉዳዩ ላይ በጋራ ተወያይተው የተስማሙባቸውን የማሻሻያ ነጥቦችና ተጨማሪ ሐሳቦች በአንድ ድምፅ ወስነው ለጠቅላይ ቤተ ክህነት በጽሑፍ እንዲልኩና ቅዱስ ሲኖዶስም የቀረቡትን የሕገ ቤተ ክርስቲያኑን አንቀጾችና ተያያዥ ሰነዶችን በሚገባ መርምሮና አጥንቶ ተገቢውን ማሻሻያ እንደሚያደርግባቸው ወስኗል።

8ኛ/ በአገራችን ኢትዮጵያ ከሁለት ዓሥርት ዓመታት በፊት በተካሔደው የሥርዓተ መንግሥት ለውጥ ምክንያት ጥንታዊው የቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያዊ ቀኖና ባለመከበሩ በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል ልዩነት መፈጠሩ ይታወቃል። በመሆኑም ይህ ጊዜ ያመጣው ሰው ሠራሽ ልዩነት ተወግዶ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነት እስኪመለስ ድረስ ጉዳዩን በገለልተኛነት በማየት እስካሁን የቆያችሁ አብያተ ክርስቲያናት አሁን ያለንበት ወቅት ሁላችንም ከምንጊዜው በበለጠ የምንቀራረብበትና በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተቃጣውን ከባድ ፈተና ለማለፍ፥ ብሔራዊውን ችግር በጋራ ለመወጣት እንድንችልና ለዚህም አብረን እንድንሠራ ቅዱስ ሲኖዶስ አሁንም በድጋሚ ጥሪውን ያስተላልፋል።

9ኛ/ በቅድስት አገራችን ኢትዮጵያና በመላው ዓለም የምትገኙ ውድ ወገኖቻችን እነሆ፥ ከጥንት ጀምሮ ላለፉት ፫ ሺህ ዘመናት ሕዝባችን በፍቅር፥ በሰላምና በአንድነት ተሳስቦ፤ እናት አገሩንና ዳር ድንበሩን አስከብሮ፥ በነጻነት የኖረ ባለ ታሪክ ሕዝብ ነው። ይሁን እንጂ ዛሬ ግን በሥልጣን ላይ ያለው አካል ሕዝባችንን በጭቆና ለመግዛት ይመቸው ዘንድ በዘር፥ በቋንቋና በሃይማኖት ከፋፍሎ ሕያው ታሪካችንን እያፈረሰና አንድነታችንን እየናደ ይገኛል። ከሁሉም በላይ ለኢትዮጵያ የታሪኳና የባሕሏ መሠረት የሆነችውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ክብሯንና ማንነቷን በየአደባባዩ በመዳፈር ልጆቿን አንገታቸውን እንዲደፉ፣ የገዛ ታሪካቸውን እንዳያውቁና በማንነታቸው እንዲያፍሩ በማድረግ ላይ ይገኛል። በመሆኑም ይህንን በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚደረገውን ድፍረት፥ የአገራችንንም ውድቀት እያዩ እንዳላዩ መሆንና ራስን ከኃላፊነት ማሸሽ ከታሪክ ተወቃሽነትና ከትውልድ ተጠያቂነት ስለማያድን በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ከስሕተት ንጹሕ የሆነ ኅሊና እንዲኖረን በሐሳብ የተራራቅን ተቀራርበን በመወያየት፥ ልዩነቶቻችንን ወደጎን በመተው እንደ ጥንቱ ኅብረታችንንና አንድነታችንን ከምንጊዜውም በበለጠ አጠንክረን ቤተ ክርስቲያናችንን ከጥፋት የምንታደግበትና አገራችንንም ከገባችበት አደጋ የምናድንበትን መንገድ በጋራ ለማመቻቸት እንድንችል ሁላችሁም "ሰላም፥ ፍትሕ፥ ነጻነትና እኩልነት ለአንዲት ኢትዮጵያና ለመላው ሕዝቧ" የሚለውን ቃል መርሕ አድጋችሁ በመተባበር በትጋት እንድትሠሩ ሕጋዊው ቅዱስ

ሲኖዶስ አደራውን በአጽንዖት ያሳስባል። በዚህ አጋጣሚ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ዛሬም እንደ ትናንቱ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አንድነትና የአባቶችን ኅብረት አጥብቀው ለሚፈልጉ ሁሉ የሰላም በሩን ከፍቶ፥ እጆቹን ዘርግቶ የሚጠባበቅ መሆኑን ይገልጻል።

፲ኛ/ በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም በሚገኙ ክርስቲያኖች ላይ ይልቁንም ደግሞ በኢትዮጵያን ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ከፍተኛ ግፍና ሰቆቃ እየበዛ በመምጣቱ ይህ ዓይነቱን ኢሰብአዊ ድርጊት በንጹሐን ክርስቲያኖች ላይ የተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚፈጸሙትን ኢሰብአዊ ድርጊት ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አጥብቆ ያወግዛል፥ ከክፉ ተግባራቸውም እንዲመለሱ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያስተላልፋል።

በመጨረሻም ፺፩ኛውን የሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ የርክበ ካህናት ጉባኤ በማስተናገድ የደከሙትን በጊዜያቸው፥ በገንዘባቸው፥ በዕውቀታቸውና በጉልበታቸው የተራዱትን በባልቲሞር፥ ሜሪላንድ የመካነ ሰላም ኢየሱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ዲያቆናት፥ ምእመናንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን ከልብ በማመስገንና ልዑል እግዚአብሔር አብዝቶ እንዲባርካቸው በመጸለይ ጉባኤው ተጠናቅቋል።

"ልዑል እግዚአብሔር አገራችን ኢትዮጵያንና መላው ሕዝባችንን ይባርክ!"

ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ
ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.
ባልቲሞር፥ ሜሪላንድ
አሜሪካ